በኢትዮጵያፌደራላዊዲሞክራሲያዊሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN CONSTRUCTION PROJECT MANAGEMENT INSTITUTE

ቁጥር
Ref.N ጠ246/ሠ-110/16
ቀን
Date 15-2-2009

አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
ADDIS - ABABA - ETHIOPIA

**ለመቀሌ ዩኒቨርስቲ**
መቀሌ

**ጉዳዩ ፡- የጥናትና ምርምር ሥራን ይመለከታል፡፡**

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት በሀገራችን ኢኮኖሚ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘውን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሪፎርም ለማምጣት፣ ሙያዊ ስነ ምግባር የጠበቀ፣ ኃላቀር አሰራሮችን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለመቀየር እና በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ባለድርሻ አካላትን አዋህዶ የሀገራችንን እድገት ለማፋጠን ራዕይ ሰንቆ የተቋቋመ መንግስታዊ ተቋም ነው፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ ኢንስቲትዩቱ በሁሉም የኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩ ቁልፍ ተዋናዮች በተግባር ተኮር ስልጠና እና ዘመናዊ አሰራሮችን እንዲሁም ቴክኖሎጂዎችን በጥናት በመለየት ቴክኖሎጂዎችን በማላመድ አቅም በመገንባት እንዲሁም የሙያ ስነ ምግባር እንዲዳብር ድጋፍ እና ክትትል በማድረግ ሂደት ዓለምአቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እንዲፈጠር የበኩሉን በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

በዚሁ መሰረት የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ህዳር 28/2008 ዓ.ም የዘርፉን ቀጠናዊ የዩንቨርሲቲ - ኢንዱስትሪ ትስስር ፎረም መመስረቱ እንዲሁም ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የተጠኑ ጥናቶችን አሰባስቦ እና አወዳድሮ በመለየት ለስድስት ጥናቶች መድረክ በማመቻቸት በዘርፉ ባለሙያዎች በማስተቸት እና አስተያየት እንዲሰጥበት መደረጉ ይታወሳል፡፡ በቀጣይም ጥናቶቹ ወደ ኢንዱስትሪው እንዲሰርፁ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም በጀት ዓመት በዩኒቨርሲቲ - ኢንዱስትሪ ትስስር አማካኝነት ለመስራት ከታቀደው ውስጥ አንዱ የሆነው በዩኒቨርስቲዎች የሚደረጉ ጥናቶችን ድጋፍ በማድረግ በጋራ መስራት ነው፡፡ በመሆኑም ኢንስቲትዩታችን ከዩኒቨርስቲዎቹ ጋር በመሆን ከዘጠኙም ትምህርት ክፍሎች ማለትም Highway Engineering, Construction management, Structural Engineering, Geotechnical Engineering, Hydraulic Engineering, Electrical Engineering, Mechanical Engineering, Industrial Engineering እና Environmental Engineering ውስጥ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ርዕሶች ዙሪያ፣

1. በወጪ ቆጣቢ የግንባታ ቴክኖሎጂዎች፣
2. ከውጭ ሀገር የምናስገባቸውን የግንባታ ግብዓቶች በሀገር ውስጥ ግብዓቶች መተካት የሚያስችል
3. የተሻሻሉ እና ወጪ ቆጣቢ ቀላል የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ዙሪያ እና
4. በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶችን የሚጠቁሙ

በመምህራን ወይም ድህረ ምረቃ ተማሪዎች እንዲሁም በ ፒ ኤች ዲ እጩዎች ሊጠኑ የታሰቡ ጥናቶችን ፕሮፖዛል ቢያንስ ስድስት የጥናት ፕሮፖዛሎች ከ10 ገጽ ያልበለጠ እንድትልኩልን እየጠየቅን በቀጣይ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተመረጡትን ፕሮፖዛሎች ውል በመፈራረም የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ከኢንስቲትዩታችን ጋር ጥናቱን በጋራ የምናካሂድ መሆኑን እያሳወቅን ፕሮፖዛል ማሳወቂያ ጊዜ እስከ ጥቅምት 25 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ዮሴፍ ብሩ ገ/ጊዮርጊስ (ዶ/ር)
ዋና ዳይሬክተር

Ethiopian Construction Project Management Institute

**ግልባጭ**
- ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
  አዲስ አበባ
- ለዋና ዳይሬክተር
- ለም/ዋና ዳይሬክተር
- ለጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት
  ኢ/ኮ/ፕ/ማ/ኢ

ማስታወሻ፡- ለተጨማሪ መረጃ 09-11 68 45 03 ለአ/ሮ ቅድስት ማሞ በመደወል መጠየቅ የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፡፡ Email:- zkid.mamo21@gmail.com